# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 167 ሃምሌ 21 2003 ገጽ 1

**ግንቦት 7 ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በእኩል የሚያይ እና ሁሉም ኢትዮጵያዊ በእኩል እንዲታይ የሚታገል ንቅናቄ ሲሆን የህግ የበላይነት የሰፈነባት፤ ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩባት፤ የዜጎቿ ሁለንተናዊ መብቶች በእኩልነት የተረጋገጠባት ኢትዮጵያን ብቻውን ወይም ከሚመስሉት ጥቂቶች ጋር ብቻ ተጋግዞ እውን ማድረግ ይቻላል ብሎ አያምንም። የምናልማት ውብ ኢትዮጵያን ለመገንባት መተባበራችን የግድ ነው ብሎ ያምናል።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በግንቦት7፣ በኦነግና በኦብነግ መካከል ተቀራርቦ የመስራት ጅመር ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል ሲሉ ዶ/ር ብርሁኑ ነጋ ገለጹ

የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ድርጅት ኢሳት ማክሰኞ ሐምሌ 19 ቀን በኒዘርላንድስ ዋና ከተማ አምስተርዳም ላይ አዘጋጅቶት በነበረው የገቢ ማሰባሰቢያ ስብሰባ ላይ በተጋባዥ እንግዳነት ንግግር ያደረጉት የግንቦት 7 ንቅናቄ ሊቀመንበር ዶር ብርሃኑ ነጋ፤ ድርጅታችን ግንቦት 7 ከኦሮሞ ነጻነት ግንባርና ከኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ግንባር ጋር ተቀራርቦ በጋራ ለመሥራት የጀመረው ጥረት የኢትዮጵያን አንድነት አስተማማኝ መሠረት ላይ ለማቆም የሚረዳ እንደሆነ ስለሚያምን አጠናክሮ እንደሚቀጥልበት አስታወቁ።

ዶ/ር ብርሀኑ በዚህ ንግግራቸው ከእነዚህ ሁለቱ ድርጅቶች ጋር ተቀራርቦ መስራትን የሚቃወሙ የአንድነት ሀይሎች ያዋጣል የሚሉትን መንገድ መከተል እንዳለባቸው ገልጸው፣ በድርጅቶች መካከል እርስ በርስ ሽኩቻ ሊኖር እንደማይገባውና ድርጅቶች ጉልበታቸውን፣ ሀይላቸውንና ጊዜያቸውን አገራቸውን በማዳን፣ አንባገነኑን ስርአት በማስወገድ ላይ ብቻ እንዲያውሉ መክረዋል።

ግንቦት7 የኢትዮጵያን አንድነት በይፋ እንደማይቀበሉ ከገለጡ ሐይሎች ጋር ከመስራቱ በፊት የኢትዮጵያን አንድነት ከሚቀበሉ ሀይሎች ጋር በቅድሚያ መስራት ነበረበት በማለት አስተያየታቸውን ለሰጡ አንድ ተሳታፊ የኦሮሞ ተወላጅና የኦነግ አባል መሆናቸውን በመግለጽ ምላሽ የሰጡ ሌላው ተሳታፊ "ኦሮሞ በዲሞክራሲና በህግ የምትመራ አገር ከተመሰረተች የሚገነጠልበት ምንም ምክንያት የለም፣ ኦሮሞ ግንድ ነው፣ ኢትዮጵያን ያለ ኦሮሞ ኦሮሞን ያለ ኢትዮጵያ ማሰብ አይቻለም በማለት" ከማንም በላይ ለአንድነት ተቆርቋሪ ነን ለሚሉ ወገኖቻችን መልዕክት አስተላልፈዋል።(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በህዝብ ላይ የአደባባይ ዝርፊያን አካሄደ፣ ከያንዳንዱ የሞባይል ቴሌፎን ተጠቃሚ ሃምሳ ብር ነጠቀ

በሰሜን አፍሪቃ ህዝባዊ አመጽ ከተነሳና በርካታ የአፍሪቃ ሃገራትን ካርበደበደ ወዲህ በያቅጣጫው ውጥረት ውስጥ በመዘፈቁ የሚያደርገውና የሚጨብጠው ጠፍቶት የቆየው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የህዝብን የትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር በሚል የለቀቀው የአባይ ግድብ ግንባታ ነጠላ ዜማ ሽያጭ የታሰበውን ያህል ሊከናወን ባለመቻሉ ከያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የሞባይል ተጠቃሚ ሃምሳ ብር እንዲቆረጥ ማድረጉን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ሪፖርት ገለጸ። እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ እንዲህ ያለውን ግልጽ የሆነ ዘረፋ የፈጸመው በማን አለብኝነትና በጉልበት የኢትዮጵያዊያንን ይሁንታ ሳያገኝና ምንም አይነት መረጃ ሳይሰጥ እንደሆነ ታውቋል።

ዘጋቢያችን ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የፈጸመውን ዝርፊያ አስመልክቶ አስተያየት እንዲሰጡት ጥያቄ ካቀረበላቸው የሞባይል ስልክ ተጠቃሚዎች አንዱ በሰጡት ምላሽ፣ እቅርብ ቀን ሞባይሌን አንድ መቶ ብር ከፍየ ሂሳብ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በኢትዮጵያ በስፋት እየታየ ያለው የትምህርት ጥራት ደረጃ ዝቅተኝነት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የጎላ መሆኑ በጥናት ተረጋገጠ

ዩ ኤስ አይ ዲ በመባል የሚታወቀው የ አሜሪካ የልማት ተራድኦ ባወጣው ጥናታዊ ጽሁፍ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ማንበብ በሚገባቸው ሰአት በብቃትና በጥራት እንደማያነቡ አጋለጠ።

ዩኤስ አይ ዲ ባወጣው በዚሁ ጥናቱ እንዳመለከተው ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙት 8 ክልሎች በሚገኙት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 80 በመቶ የሚሆኑ ህጻናት ማንበብ በሚገባቸው እድሜ ማንበብ እንደማይችሉ ታውቋል። እንደ ጥናታዊ ጽሁፉ ሪፖርት ይህ አሀዝ ወደ ሲዳማ ክልል በሚመጣበት ጊዜ 100 በመቶ እንደሚደርስ ጥናቱ አሳይቷል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ለብሄር ብሄረሰቦች መብቶች ጠበቃ ነኝ በማለት በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ አድርጊያለሁ ቢልም፣ በሲዳማ ከ70 በመቶ፣ በትግራይ ከ57 በመቶና በቤንሻንጉል ጉሙዝ 54 በመቶ የሚሆኑ የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች የሃገራቸውን ታሪኮች አንብበው መረዳት ፈጽሞ እንደማይቺሉ አጋልጧል።

ከትምህርት ጥራት ጋር በተያያዘ ሰፊ ጥናት ያካሄደው ዩ ኤስ ኤድ በክልሎች ያለው የመጽሀፍ አቅርቦት በሚመለከት ያካሄደው ጥናት (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ግዜ

## በኢትዮጵያ ሚሊየኖች ይራባሉ፣ ነገር ግን የውጪ ሃገራት ኢንቨስተሮች በሺሆች የሚቆጠር ቶን እህል ኤክስፖርት ያደርጋሉ ተባለ

በርካታ ሚሊየኖች በርሃብ አለንጋ እየተገረፉባት በምትገኘው ኢትዮጵያ የውጪ ሃገራት ኢንቨስተሮች በርካታ ሺህ ቶን የጥራጥሬ ምግብ እህልን እያመረቱ ለትርፍ ወደ ውጪ ሃገራት ኤክስፖርት እያደረጉ መሆኑ የሚያሳዝን እውነታ ነው በማለት ስዊስ ኢንፎ በመባል የሚታወቅ የዜና አውታር ገለጸ። እንደ ስዊስ ኢንፎ ዘገባ በሃገሪቱ ምእራባዊ ክፍል የህንድ ኢንቨስተሮች ገና እድሚያቸው ለስራ ያልደረሱ ህጻናትን ሳይቀር በጉልበት እያሰሩና እየረገጡ ትርፍ ያግበሰብሳሉ ብሉአል።

በህንድ ኢንቨስተሮች በተያዘው የሸንኮራ አገዳ ተክል ማሳ በመገኘት የታዘበውን የዘገበው የስዊስ ኢንፎ ጋዜጠኛ እንደገለጸው የአየሩ ሙቀት 40 ዲጊ ሴንቲግሬድ በደረሰበት በዚሁ የእርሻ ማሳ የስምንት አመቱ ለጋ ህጻን በጉልበቱ ተንበርክኮ አረም ያርማል፣ ከሁአላው ደግሞ የህንዱ ባለሃብት ቆሞ ህጻኑ እያንዳንዱአን አረም ሳያስቀር እያረመ መሆኑን በመጎማለል ይቆጣጠራል ካለ በኋላ፣ የሚገርመው ነገር ለዚህ ህጻን የጉልበት ስራ በቀን የሚከፈለው ባለሃብቱ ለአረም መድሃኒት ከሚያወጣው ውጪ በጣም ያነሰና ዜሮ ነጥብ ስምንት ሶስት ዩሮ የሆነ ዝቅተኛ ገንዘብ ነው በማለት በሃዘን ገላጹአል።

በኢትዮጵዩአ ከ12 ሚሊዮን በላይ ዜጎች በርሃብ አለንጋ እየተገረፉ እንደሆነ ራሱ ዘረኛው አገዛዝ በይፋ የገለጸ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፣ ከነኚህ ረሃብተኞች ውስጥ ወደ አራት ነጥብ ሁለት ሚሊየን የሚሆኑት በአስሸቺኳይ ጊዜ ርዳታ የሚገኙ ናቸው። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የከፍተኛ ትምህርት ተቋዋማት የትምህርት ጥራት ደረጃ እጂግ አሳሳቢ ሆነ፣ ተመራቂዎች ምንም ቁም ነገር ሳንይዝ ለምረቃ በቃን አሉ

በያዝነው ዓመት እጂግ በርካታ ተማሪዎች በተለያዩ የትምህርት መስኮች ትምህርታቸውን ተከታትለው በተለያዩ ደረጃዎች በመመረቅ ላይ ያሉ ሲሆን የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ያነጋገራቸው ምሩቃን በሰጡት አስተያየት ምን እንደተማርን ሳናውቀውና እዚህ ግባ የሚባል እውቀት ሳንጨብጥ ለምረቃ በቃን፣ ይህም እኛን እያሳፈረንና እያሸማቀቀን ይኖራል በማለት ለዚህ ያበቃቸውን ሥርዓት አመራሩ ።

ዘጋቢያችን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ምረቃ ሥነ ሥርዓት በመገኘት ካነጋገራቸው ተመራቂዎች ውስጥ በኢኮኖሚክስ ትመህርት መስክ በኤክስቴንሽን የመጀመሪያ ዲግሪዋን ያገኘት ስሟ እንዳይገለጽ የጠየቀች ወጣት፣ በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ብቃት ያላቸው መምህራንና በቂ የማስተማሪያ መሣሪያዎች እጥረት ጎልቶ መኖሩን መንግሥት ተብዬው አገዛዝ እያወቀው ምረቃ በአላችን ላይ የተገኘው የወያኔ ሹም ጁኔዲን ሳዶ የትምህርት ጥራት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሶአል የሚል ድስኩር መልሶ ለኛው ለተጎጂዎች ማሰማቱ እጅግ የሚያበግን ነው ብላለች። ወጣቷ በመቀጠልም፣ አገራችን ውስጥ ስራ በመፈለግ ራስን ለማስተዳደር አንደኛው መንገድ ራስን በትምህርት የተሻለ ደረጃ ላይ ማስቀምነጥ እንደነበር ገልጻ ባሁኑ ወቅት ይህ ሁሉ ቀርቶ ስራ ማግኘት በፓርቲ አባልነት፣ በዘመድ አዝማድና በሌሎችም አሳዛኝ መንገዶች በመሆኑ ትምህርቷን አጠናቃ በዲግሪ መመረቁ በራሱ ምንም ትርጉም ሊሰጣት እንደማይችል በምሬት ገልጻለች። አገሪቷ ውስጥ በተንሰራፋው ዘረፈ ብዙ ችግሮች ምክንያት የተሻለ እውቀትና ልምድ ያላቸው አገራቸውን ጥለው እየተሰደዱ የትምህርት ጥራት እንዴት ማስጠበቅ እንደሚቻል ማወቅ ይቸግራል ያለቺው ወጣት እንደአሸን የፈሉ የዘመናችን ዩኒቨርሲቲዎች ደረጃ ታላላቆቻችን ከነበሩበት የሁለተና ደረጃ በ እጅጉ እንደሚያንስ ህብረተሰቡ ተገንዝቦታል ብላለች። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## አረመኔው የወያኔ አገዛዝ ከኤች አይቪ ቫይረስ ጋር የሚኖሩ የቴሌ ሠራተኞችን መድሃኒት እንዳያገኙ ከለከለ

ከኢትዮ ቴሌኮም መሥርያ ቤት ሕግና ሥርዓት ሳይጠበቅ ሕገወጥ በሆነ መንገድ ከሥራ ገበታቸው ላይ ከተባረሩት መካከል፣ ከኤችአይቪ/ኤድስ ቫይረስ ጋር የሚኖሩ ሠራተኞች መድኃኒት እንዳይወስዱ መከልከላቸውን በማስረዳት ቦርዱ እንዲታደጋቸው መጠየቃቸውን ለአረመኔው አገዛዝ ቅርበት እንዳለው የሚነገርለት ሪፖርተር ጋዜጣ ዘገበ፡፡

ከኤችአይቪ/ኤድስ ቫይረስ ጋር የሚኖሩት ሠራተኞች ለኢትዮ ቴሌኮም ቦርድ "ፋታ የማይሰጥ ማመልከቻ አለን" ይታይልን በማለት ሊያስረዱ ሲሞክሩ፣ ቦርዱ "በቃለ መሀላ ያስገባችሁት ማመልከቻ ስላለ ከዚህ የተለየ ምን ትናገራላችሁ?" የሚል ዘለፋ የተሞላበት ምላሽ የተሰጣቸው መሆኑንም ይህው ዘገባ አመልክቱአል። እንደ ሪፖርተር ዘገባ ከኤችአይቪ/ኤድስ ጋር ከሚኖሩት ሠራተኞች አንዷ ለቦርዱ እንደገለጹት፣ ሊደርስባቸው የሚችለውን መድሎዎና መገለል በመቋቋም "ትውልድ ይዳን በእኛ ይብቃ" ብለው ራሳቸውን አጋልጠው ሕዝብን ሲያስተምሩ ቆይተዋል ካለ በሁአላ ሐምሌ 14 ቀን 2003 ዓ.ም. ወደ ኢትዮ ቴሌኮም ክሊኒክ መድኃኒት ለመውሰድ ሲሄዱ አይገቡም ተብለው መከልከላቸውን መናገራቸውን ገልጹአል:: (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ለዴሞክራሲና ለእኩልነት መረጋገጥ በጋራ የምናደረገውን ትግል የአንድነታችን መሠረት እናድርግ

የግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ራዕይ ሁሉንም የኢትዮጵያ ዜጎች፤ ሁሉንም የኢትዮጵያ ማኅበረሰቦች እና ሁሉንም የኢትዮጵያ አካባቢዎች ታስቦ የተቀረፀ ነው።

የግንቦት 7 ተልዕኮ በሃገራችን ውስጥ አካባቢ ለይቶ፤ ዘውግንና ሃይማኖትን አማርጦ ተግባራዊ እንዲሆን የተቀረፀ አይደለም።
ግንቦት 7፤

- “ህዝብ የስልጣን ባለቤት መሆን ይኖርበታል” የሚለው፣
- ነፃ ተቋማት እንዲገነቡ የሚጥረው፣
- ፍትህ፣ ነፃነትና ዲሞክራሲ እንዲኖር የሚታገለው በመላው አገራችን - ኢትዮጵያ - ውስጥ ነው።

እነዚህ ታላላቅ ግቦች በአንድ ወይም በጥቂት የአገራችን ክፍሎች ተሳክተው በሌላ የአገራችን ክፍል ባይሳኩ የግንቦት 7 ተልዕኮ ተሳካ አይባልም።

ግንቦት 7 ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በእኩል የሚያይ እና ሁሉም ኢትዮጵያዊ በእኩል እንዲታይ የሚታገል ንቅናቄ ሲሆን የህግ የበላይነት የሰፈነባት፤ ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩባት፤ የዜጎቿ ሁለንተናዊ መብቶች በእኩልነት የተረጋገጠባት ኢትዮጵያን ብቻውን ወይም ከሚመስሉት ጥቂቶች ጋር ብቻ ተጋግዞ እውን ማድረግ ይቻላል ብሎ አያምንም። የምናልማት ውብ ኢትዮጵያን ለመገንባት መተባበራችን የግድ ነው ብሎ ያምናል።

እርግጥ ነው ግንቦት 7 በተቻለው ሁሉ ራሱን ጠንካራና በህዝብ ውስጥ ተቀባይነት ያለው ድርጅት ለማድረግ ይሰራል። ይሁን እንጂ የሃገራችን የዴሞክራሲና የነፃነት ትግል ስፋት ያለውን የኅብረተሰቡን አባላት እና በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ አመለካከቶችንና ፍላጎቶችን አካቶ ካልተንቀሳቀሰ የኢትዮጵያ ህዝብ ዘላቂ ድል ሊቀዳጅ የሚችልበት እድል እጅግ ዝቅተኛ ነው ብሎ ያምናል። የተለያዩ አመለካከቶችንና ፍላጎቶችን የሚያንጸባርቁ የፖለቲካ ኃይሎችን በማስተባበር የሚደረግ ትግል መስዋዕትነቱን አነስተኛ፤ ትግሉን ደግሞ ቀልጣፋ ከማድረግ አልፎ በወያኔ ግፈኛ አገዛዝ መቃብር ላይ ለሚቆመው ዴሞክራሲያዊ መንግሥታዊ ሥርዓት መሠረት የሚሆነውን ሃገራዊ ሰላም ያስገኛል ብሎ ያምናል። በትግሉ ሂደት የሚፈጠረው መግባባት በድል ማግስት ለሚጀመረው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና የሽግግር ሂደት አመቺ ሁኔታዎችን ይፈጥራል ብሎ ያምናል። ባለንበት ሁኔታ የተለያዩ አመለካከቶች ያላቸው ቡድኖች በከፍተኛ ትዕግስትና መግባባት አንዱ ሌላውን ሳያገል መሄድ ካልቻሉ ትግላቸው ከወያኔ ጋር መሆኑ ቀርቶ እርስ በርሳቸው ይሆናል የሚል ስጋት አለው። ከእንዲህ አይነቱ የተቃዋሚዎች ሽኩቻ በላይ ወያኔን የሚያስፈነድቀው ነገር የለም፤ እስካሁንም በኢትዮጵያዊያን ጫንቃ ላይ እንዲቆይ ያደረገው ይኸው ነው።

ግንቦት 7፣ ዛሬ በሃገራችን ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ፍላጎቶችና አመለካከቶች ያላቸው የፖለቲካ ቡድኖች፣ ማኅበረሰቦችና ዜጎች ሁሉ የወያኔ የመብት ረገጣ፣ የስደት፣ የግድያና የዝርፊያ ሰለባ ሆነዋል ብሎ ያምናል። ይህን ሃቅ ሆኖ እያለ ሁሉም በየግሉ የራሱን ፍላጎት ለማስፈጸም የሚያደርገው ጥረት የጋራ ባርነት፣ ውርደትና ስቃይ የሚያተርፍልን መሆኑ ብዙሃኑ የሃገሪቱ ህዝብ እየተረዳው መጥቷል የሚል እምነት አለን።

ግንቦት 7 ይህ የጋራ የመከራ እጣ ከታሪክ እስረኛነት፤ ከድርጅቶችና ከመሪዎች ግላዊ ፍላጎቶች፤ከምንከተለው የፖለቲካ ርዕዮተዓለምና ቀኖና በላይ ገዝፈን እንድንገኝ ያደርገናል የሚል እምነት አለው። ይህ እምነት ግንቦት 7 በአጠቃላይ በሃገር ጉዳይም ይሁን በአንድ ማኅበረሰብ ጉዳይ ያገባኛል ከሚሉ የፖለቲካ ቡድኖች፤ የሲቪክ ድርጅቶች፤ ከትልቁ ሆነ ከትንሹ፤ በርካታ ተከታይ አለኝ ከሚለው ሆነ ተከታይ የለውም ከሚባለው ጋር በጋራ ለመሥራት የሚያደርገውን ጥረት አጥብቆ እንዲገፋበት የሚያበረታተው ሆኖ አግኝቶታል።

ግንቦት7 በአመለካከት በሚቀርቡትና በማይቀርቡት መሃል ጎራ ለይቶ ከሁሉም የኅብረተሰባችን አካላት ጋር የጀመረውን ግንኙነት የሚያጠብበት ምክንያት የለውም። በአስቸጋሪ ሁኔታ እየገነባው ያለውን የመገናኛ ድልድይ ሰብሮ ከዚህኛው ወይም ከእዛኛው የፖለቲካ ቡድን ውስጥ ተካቶ አንዱን አግልሎ ሌላውን አቅፎ የሚሄድበት በቂ ምክንያት የለም።

በወያኔ ላይ ተቃውሞ አለን የሚሉ ቡድኖች በሙሉ ደግመው ደጋግመው ሊያስቡበት የሚገባ ጉዳይ እርስ በርሳቸው ተጨባጭነት ባላቸውም ሆነ በሌላቸው ጉዳዮች በመነታረክ የሚያጠፉት ጊዜ ለጋራ ውድመት እንጂ ለግል ድል የማያበቃቸው መሆኑን ነው። በተቃዋሚ ድርጅቶች መሃል ሰፊ ስምምነት መፍጠር እንኳን ባይቻል የሚስማሙ ኃይሎች ተባብረው በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ ይዘምታሉ እንጂ ትግላቸውን ከሌሎች ታቃዋሚ ድርጅቶች ጋር አያደረጉም።

እንኳንስ ተቃዋሚዎች በተዳከሙበት በአሁኑ ጊዜ ቀርቶ ጠንካሮች ሁነው ቢሆንም ኖሮ ሁሉንም ችግሮች በአንድ ጊዜ ለመፍታት መሞከር አዋቂነትንና አርቆ አሳቢነትን አያመለክትም።

ግንቦት7 ለድክመቱም ሆነ ለጥንካሬውም ተጠያቂ የሚያደረገው እራሱን ነው። የራሱን ድክመት ከራሱ ውጭ ባሉ አካላት ላይ አያላክክም።

ግንቦት 7 የሃገራችንን፣ የአካባቢያችንን የፓለቲካ ሁኔታ፤ ወያኔን እንቃወማለን የሚሉ ድርጅቶችን ጥንካሬና ድክመት በሚገባ መርምሮ በትብብር ጉዳይ ላይ የወሰደው አቋም አለው። ሌሎች ድርጅቶችም ይህንኑ አቋም፣ አመለካከትና እምነት እንዲጋሩ ጥረት ያደርጋል። ከዚህ ውጭ ግን የምለውን ካልሰማችሁ ብሎ የወያኔ ግፈኛ አገዛዝ ሰለባ ከሆኑ ወገኖቹ ጋር የሚያቃርነውና የሚያጣላው ምክንያት ከቶውኑ አይኖርም። ግንቦት 7 የሃገርና የዜጎች ጠላት ከሆነው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ አይኑን አንስቶ የሚያሳርፍበት ቦታ የለውም።

የጋራ የሆነች አገራችንን በጋራ ለመገንባት የወንድሞቻችንና የእህቶቻችንን ቅሬታዎች የማድመጥ ትዕግሥትና ብልህነት ይኑረን። የዲሞክራሲ ሥርዓት የሚያረጋግጠው እኩልነት የአንድነታችን መሠረት እናድርግ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## በግንቦት7፣ በኦነግና በኦብነግ መካከል ተቀራርቦ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ኢሳት ባዘጋጀው በዚህ የገቢ ማሰባሰብ ስብሰባ ላይ ከተሳተፉ ኢትዮጵያዊያን፤ ግንቦት7 ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ተቀራርቦ በጋራለመታገል የሚያደርገውን ጥረት በማድነቅ፤ ከኦነግና ኦብነግ ጋር ለመቀራረብ የሚደረገው ጥረት ዛሬ እንዳልተጀመረና የአንድነት ሀይሎች ነን የሚሉ የተለያዩ ድርጅቶች ለረጂም ጊዜ ሲደክሙበት የቆዩ መሆኑን፤ አሁን ግንቦት7 ከእንዚህ ሁለቱ ደርጅቶች ጋር ለመስራት በመወሰኑ ቀደም ሲል ተመሳሳይ ሙከራ ያካሂዱ የነበሩ ለምን የተቃውሞ አቧራ ለማስነሳት እንደፈለጉ እንደማይገባቸው የተናገሩ ይገኙበታል።

በመጨረሻም ኢሳት በጠራው የገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅት የኢሳት የሆላንድ የድጋፍ አስተባባሪ ሰብሳቢ የሆኑት አቶ ወንዶሰን ገብረህይወት ኢትዮጵያውያን ኢሳትን እንዲደግፉ ጥሪ አቅርበው ይህን የተሳካ ዝግጅት ለማዘጋጀት እገዛ ላደረጉት ሁሉ በኢሳት ስም ከፍተኛ ምስጋና በማቅረብ የገቢ ማሰባሰቢያው ዝግጅት እንደተካሄደ ከኢሳት ያገኘነው ዘገባ ገልጾአል።

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በህዝብ ላይ የአደባባይ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ማስሞላቴን በትክክል አውቃለሁ፣ ነገር ግን ባልተገነዘብሁት ሁኔታ ባጭር ጊዜ ውስጥ የነበረው ባላንስ አለቀ፣ ሁኔታው ገርሞኝ ጓደኞቸን ስጠይቅ ተመሳሳይ ችግር እንዳለባቸው ነገሩኝ። በመጨረሻም ለምን እንዲህ እንደሆነ ስንከታተል፣ ቴሌ ውስጥ የሚሰራ ጓደኛችን የዘረፋ ሚስጥሩን አጫወተን ብለዋል። በመቀጠልም፣ እኛ በተለይም በሃገር ውስጥ የምንገኝ ኢትዮጵያዊያን እጅግ የሚያሳፍር፣ የሚያሳዝንና አሳሳቢ በሆነ ወቅት ላይ እንገኛለን። የወያኔ አገዛዝ በኛ ላይ አልፈጸመዉም የሚባል ግፍ መናገር የሚቻል አይመስለኝም። ሁሉንም ፈጽሞብናል። አሁን የምንገኘው በሞትና በህይወት መካከል ነው። እናም ወይ አይናችን እያየ መሞት እንዲሁም ልጆቻችንን እጂግ አሳዛኝ ለሆነ ጭራቅ አገዛዝ አሳልፈን መስጠት፣ ወይንም ደግሞ ከዚህ ዘረኛ አገዛዝ አፈና ለመላቀቅ በአንድነት ሆ ብለን መነሳትና ወያኔን ማስወገድ በማለት ምላሻቸውን አጠቃለዋል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የአባይ ግድብ ግንባታን ያለማንም የውጭ ሃይል እገዛ ማከናወን እቺላለሁ፣ 80 ቢሊየን ብር የሚወደኝ የኢትዮጵያ ህዝብ ያዋጣል በማለት በአደባባይ ሌት ከቀን የለፈለፈ ቢሆንም፣ ያልሰበሰበውን ገንዘብ ሰብስቢያለሁ በማለት የተጋነነ ቁጥር የሚያቀርበው ዘረኛ አገዛዝ ራሱ የተናገረውና እስካሁን የሰበሰበው ገንዘብ ከሶስት ቢሊየን ብር በታች መሆኑ ለወያኔ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ይናገራሉ።

## በኢትዮጵያ በስፋት እየታየ ያለው የትምህርት ጥራት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

እንደሚያመለክተው አቅርቦቱ ከአንዱ ክልል ወደ ሌላው በእጅጉ እንደሚለያይ ያመለክታል። በዚህም መሰረት የመጻህፍት አቅርቦት በክልል ደረጃ ሲታይ በሶማሊያ 42 በመቶ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ደግሞ 59 በመቶ የሚሆኑት የሚያነቡት መጽሀፍት ያላቸው ሲሆን፣ በትግራይ ግን 95 በመቶ የሚሆኑ ተማሪዎች የሚይነቡት መጽሀፍት አላቸው። ይሄው ጥናት አያይዞ በአማራ 70 በመቶ በሲዳማ ደግሞ 61 በመቶ ተማሪዎች የራሳቸው መጽሀፍት አላቸው ብሏል።

ዩ ኤስ ኤይድ ያካሄደውን ጥናት ሲያጠቃልል፣ በኢትዮጵያ የሚገኙ ተማሪዎች ለሁለትና ሶስት አመታት ትምህርት ቢከታተሉም አብዛኞቹ መሀይም እንደሆኑ ናቸው ካለ በኋላ የተማሪዎችን የማንበብ ብቃት ለማሳደግ ተጨማሪ መጽሀፍት እንዲሰራጩ፣ ውስብስብ የሆነው የቋንቋ ችግር እንዲፈታ፣ የመምህራን ብቃት እንዲያድግ ጥረት እንዲደረግና ትምህርት ንባብ ከአንደኛና ከሁለተኛ ክፍል እንዲጀመር ሀሳብ አቅርቧል።

በኢትዮጵያ በተለይም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመምህራን ብቃት ማነስ ችግርና ለትምህርት አስፈላጊ በሆኑ ቁሳቁሶች እጥረት ምክንያት ተመራቂዎች በየተማሩባቸው የትምህርት መስኮች ምንም አይነት በቂ እውቀትን እንደማይጨብጡና ለስራም ብቃት እንደማይኖራቸው ራሳቸው ተመራቂዎች መናገራቸውን መዘገባችን ይታወሳል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ለምእራባዊያን የተጋነነ አሃዝን ሪፖርት በማድረግ በጤናና በትምህርት መስክ የሚሊኒየሙን የልማት ግቦች አሳክቻለሁ በማለት ለማደናገር ቢሞክርም ፣ በሁሉም ዘርፍ እየተደረጉ ያሉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አገሪቷ በጥራትም ሆነ በአቅርቦት ገና ብዙ ያልተሠሩ ነገሮች እንዳሉ ይታወቃል።

# መለስ ዜናዊና የቀደሙት ነገስታት

ከዝግጅት ክፍላችን

በ1808 ዓ.ም እንግሊዞች በአጼ ዮሃንስ እየተመሩ መቅደላ ድረስ ገስግሰው ደርሰው ከአጼ ቴዎድሮስ ጋር ጦርነት ገጥመው ረቷቸው።አጼ ቴዎድሮስም ለባእድ እጄን አልሰጥም ብለው በገዛ ሽጉጣቸው ራሳቸውን ገደሉ። ይህም ጀግነንት ሆኖ ተቆጥሮላቸው እስከ ዛሬ ባለው ትውልድ ዘንድ ሲዘከር ይኖራል።

አጼ ቴዎድሮስ በገዛ ሽጉጣቸው ራሳቸውን የገደሉ ግዜ በወቅቱ ከነበሩ ባለ ቅኔዎች አንዱ የሚከተለውን ቅኔ ተቀኘላቸው፤

*በመቅደላ አፋፍ ላይ ጩኸት በረከተ፤*
*የሴቱን አናውቅም ወንድ አንድ ሰው ሞተ።*
*ኢያችሁት ወይ ያንበሳውን ሞት፤*
*በሰው እጅ መሞትን ነውር አድርጎት።*

በወቅቱ የንጉሱ ጀግንነት ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ ታውቆ ስለነበረ የተደረሰላቸው ግሩም ቅኔ ነው።

የጦርነቱ ምክንያት ንጉሱ እጃቸውን ይዘው ያሰሯቸው የእንግሊዝ ዜጎች ነበሩ። እንግሊዞች ዙሪያቸውን ከበው ባስጨነቋቸው ግዜ ካጠገባቸው ከቆሙት አንዱ "ጃንሆይ እንግዲህ መሞታችን ካልቀረ የዚህ ጦርነት ምክንያት የሆኑትን እነዚህን የታሰሩትን እንግሊዞች መዥመሪያ ገድለን እኛም ሄደን እንሙት" ሲል አማከራቸው።

አጼ ቴዎድሮስ ግን *"ያገሬን ሕዝብ አንድ ለማድረግ እኔ ያጉላላሁት አንሶ እነዚህን ገድየ ሕዝቤን በባእድ እጅ እንዲጠቃ አላደርግም"* ብለው መለሱለት። ይሄም ሃሳባቸው እስከ ዛሬ ሲያስመሰግናቸው ይኖራል። ጀግና እንዲህ ነው። በጥላቻ መካከል ፍቅርን፤ በጭካኔ ውስጥ ርህራሄን ማሳየት የጀግና ሰው ተግባሩ ነው።

ከጀግኖች መካከል የማይመደበው መለስ ዜናዊ ቢሆን ኑሮ ሊያደርግ የሚችለውን ሁላችንም እናውቃለን። ድህረ ምርጫ 97 ድምጻችን ይከበር ብለው አደባባይ የወጡትን ንጹሃን ለሥልጣኔ ስጋቶች ናቸው በሚል ከደቂቅ እስከ ሊቅ ማስፈጀቱን አናስታውሳለን። እንባቸውን እየዘሩ ባለቤቴን አትውሰዱብኝ እያሉ ሲለምኑ የነበሩትን ወ|ሮ እቴነሽን ልጆቻቸው ፊት በጥይት ግንባራቸውን ተደብድበው እንዲሞቱ ቀጭን ትእዛዝ ሰጥቶ የንጹሃን ደም ማፈሰሱን አንዘነጋውም። የአቤል ደም ከምድር ወደ ሰማይ እንደሚጮህ ሁሉ የ10 አመቱ ህጻን ያሲን ደም እስከ ዛሬ ካዲስ አበባ ምድር ወደ ላይ ወደ ሰማይ እየጮኸ መሆኑንም እያዳመጥን ነው። እንደመለስ አይነቱ ወይ ከጀግንነት አለያም ከፈረሃ እግዜአብሔር አንዱንም ያልተቸረ ው ስልጣን ላይ እስካቆየው ድረስ በወገንና በአገር ላይ ምንም የከፋ መከራ ቢመጣ የማይፈጽመው ዓይነት ወንጀል እንደሌለ በስልጣን ዘመኑ ያየነው ነው።

የዛሬው ሃተታችን የአጼ ቴዎድሮስን ታሪክ መዘከር ወይም መለስ ዜናዊን ከእነርሱ ጋር ማወዳደር አይደለም። ይልቁንም መለስ ዜናዊ በቅርቡ በዚያ ልቅ አንደበቱ በራሳቸው ዘመን ስለአገራቸው ወቅቱ የፈቀደላቸውን መልካም ነገር ሠርተው ስለአለፉት የተናገረውን ነውር ህዝቡ ልብ እንዲለው ለማሳሰብ እንጂ።

በመጀምሪያ ደረጃ መለስ ዜናዊ ቀጥሮ ሰው የሚያደርግ ስብእናቸውን ገፍፎ ለሚያዋርዳቸው ጋዜጠኞች እናዝናለን። በመለስ ዜናዊ ዘመን በመንግስት በጀት ተቀጥረው የሚሰሩ ጋዜጠኞች እንደ ህጻን ልጅ ጥያቄ ተዘጋጅቶ እየተሰጣቸው እንዲጠይቁ ይደረጋል እንጂ ህዝቡ ማወቅ ያለበትን ወይም ደግሞ ጋዜጠኛው ራሱ ሂሊናው የሚያዘውን ለመጠየቅ እድሉ የለውም።እንዲህ አይነት ውረደትን ለብዙ ግዜ መሸከም አንችልም ብለው አገር ጥለው የወጡ የራሱ ጋዜጠኞች የነገሩን እኛም የምናውቀው እውነት ነው።

እናም መለስ ዜናዊ ጥያቄ አዘጋጅቶ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁኝ አለ "የቀድሞ ትውልድ መጥፎ አሻራዎች ምንድ ናቸው?" ። ይህ ሰው የዚያችን አገር ታሪክ ማዋረድና ምንም በጎ ነገር እንዳልተሰራ አድርጎ ለማቅረብ ካለው ምኞት የተነሳ ከጥሩ አሻራዎች ይልቅ መጥፎ አሻራዎችን ፈለጋ ላይ ግዜውን በከንቱ ያጠፋል። መለስ ዜናዊ ራሱ ላዘጋጀው ጥያቄ እንዲህ ሲል መልስ ሰጠ ለምሳሌ አለ "ለምሳሌ አጼ ቴዎድሮስ መድፍ መስራታቸው "tragedy" ወይም ደግሞ አሰቃቂ ስህተት ነበር" አለ። በዚህም ሳያበቃ "አገሪቷን አንድ ለማድረግ ይከተሉት የነበረው አቅጣጫ የጦርነት ነበር"። ስለሆነም እንደ መጥፎ አሻራ ሲጠቀስ ይኖራል አለ። ይታያችሁ አገራችን ኢትዮጵያን በሃይል ለመቀራመት በወቅቱ ያሰፈሰፉትን የውጪ ቅኝ ገዢዎችን ለመመከት የሚያስችል ዘመናዊ የጦር መሳሪያ ባለቤት ለመሆን መነሳትን ነው እንደወንጀል ቆጥሮ "tragedy" ነው የሚለን። እንግሊዞችን መርቶ ቴዎድሮስን በማስገደል በርሳቸው እግር የተተኩትንና ስለአገር አንድነት ቴዎድሮስ የሄዱበትን ሁሉ መንገድ ስለመጓዛቸው ታሪክ የሚያስታውሳቸው አጼ ዮሐንስን በተመለከተ መለስ እስከዛሬ ምንም ሲያወራ አለመሰማቱ እንቆቅልሽ ነው።

ወደ ዋናው ነጥባችን ስንመለስ መለስ ዜናዊ በዚህ ዙሪያ የሰጠውን ቃለ መጠይቅ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን የተከታተለ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሰውየውን ጤነኛ መሆን መጠራጠሩ አይቀርም። በዚህ ረገድ መለስ ዜናዊ ፍጹም ጤነኛ ነው። የሚናገረውም አስቦበትና አውቆት ነው።ዓላማውም አንድና አንድ ነው። ብዙዎች የሚኮሩበትንና ጀግንነታቸው በብዙዎች ዘንድ የታመነለትን አጼ ቴዎድሮስን ማንቋሸሽና ማዋረድ። ለነገሩ በዚያ ዘመን መለስ ዜናዊ በአጼ ቴዎድሮስ እግር ቢሆን ኑሮ ምን ታደርግ ነበር ተብሎ ቢጠየቅ ምን ብሎ እንደሚመልስ አድማጭ ልብ ይበል።መቸስ ጋዜጠኛዋ እንዲህ ዓይነቱን ጥያቄ ለመጠየቅ የሂሊና ነጻነት የላትምና ጥያቄው አለመነሳቱ ደግ ሆነ። ለማንኛውም መለስ ዜናዊና ድርጅቱ አጼ ቴዎድሮስን የማንቋሸሽ ምንጩ ለአማራ ህዝብ ካለው ሥር የሰደደ ጥላቻ የተነሳ እንጂ ሌላ አይደለም። ነፍጠኛ ወይም ደግሞ ትምክህተኛ እየተባሉ በመለስ ልቅ አንደበት ከሚሰደቡ ሰዎች መካከል አንዱ አጼ ቴዎድሮስ ናቸው። ይህን ጥላቻውን የሚገልጥበት መንገድ ፈልጎ ያገኘው የንጉሱን በጎ ሥራ"tragedy" ወይም አሰቃቂ ስህተት ብሎ በማንቋሸሽ ነው።

በዚያ በጨለማ ዘመን ጉልበት ያለው ሁሉ እየተነሳ ለእኔ ካልገበራችሁ በክልሌ እንዳትደርሱ እያለ በየቀየው ነግሶ በሚያስቸግርበት ወቅት አገሪቷን አንድ ለማድረግ አጼ ቴዎድሮስ ሃይል ተጠቀሙ ብሎ መውቀስ የመለስን ወደር ያጣ ጥላቻ ከማሳየት ውጪ ሌላ የሚፈይደው ቁም ነገር የለም። አጼ ቴዎድሮስ በጎ ራእይ ይዘው ያለ ግዜያቸው የተፈጠሩ ከደመናው ባሻገር የጸሃይ ብርሃንን ማየት የሚችሉ ሩቅ አሳቢ መሪ ነበሩ። ኢትዮጵያችንን ትልቅ ለማድረግና በወቅቱ ከሚደረገው አፍሪቃን የመቀራመት አደጋም አገሪቷን ለመታደግ መድፍ ለመሥራት መጣራቸው በግዜው ማድረግ የሚገባቸው ወሳኝ ነገር እንጂ "ትራጄዲ" ወይም ደግሞ "አሰቃቂ" ስህተት ተብሎ ሊጠቀስ የሚችል ክስተት አይደለም። ይልቁንስ ትራጄዲ ተብሎ ሊጠቀስ የሚገባው ከ4 ነጥብ 5 ሚሊዮን ህዝብ በላይ አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ በሚፈልግበት ረሃብ ላይ ባለበት በዚህ በያዝነው አመት ከአንድ መቶ ሚሊዮን ዶላር በላይ አውጥቶ ሁለት መቶ የጦር ታንኮችን መግዛት ነው። ትራጄዲ የሚባለው ህዝቡ በርሃብ እያለቀ ባለበት በዚህ ክፍ ወቅት ከ8.4 ቢሊዮን ዶላር በላይ ካገር አሸሽቶ በውጭ ባንኮች መደበቅ ነው። ትራጄዲ የሚባለው አጼ ቴዎድሮስ በባዶ እግራቸው ከጫፍ ጫፍ ደክመው ሊገነቡ የሞከሩትን ትልቅ ኢትዮጵያ ለማፍረስ መጣር ነው። ትራጄዲ ማለት እንደ መለስ ዜናዊ ዓይነት ጥቁር ሞሶሎኒ በምንሊክ ቤተመንግስት መቆናጠጡ እንጂ የአጼ ቴዎድሮስ መድፍ ለመስራት መሞከር አይደለም።

መለስ ዜናዊ የጣቱን ቅሰራ በአጼ ቴዎድሮስ ላይ ብቻ አያበቃም።አጼ ዮሃንስን ዘሎ አጼ ምንሊክንም ሊያጣጥል ሞክሯል። አጼ ዮሃንስን ያላነሳው አለምክንያት አይደለም ለንጉሱ ልዩ ፍቅር ያለው መስሎ በመታየት የትግራይን ሰዎች ደስ ያሰኝ መስሎት ነው።እውነቱ ግን መለስ ዜናዊ አጼ ዮሃንስ የሞቱለትን የደም መሬት ለደርቡሾች ወይም ለሱዳኖች አሳልፎ በመስጠት ለኢትዮጵያው ንጉስ አጼ ዮሃንስ ያለውን ብርቱ ጥላቻ በተግባር አሳይቷልና በመለስ ቶንኮል የተሞላበት ስልት የሚታለል ካለ ራሱ የፈጠራቸው ሆድ አደሮች ናቸው እንጂ ለእውነትና ለእኩልነት የቆሙ የትግራይ ተወላጆች በዚህ ርካሽ ምኞት የሚታለሉ አይሆንም።

አጼ ምንሊክን እንዲህ ሲል ያንቋሸሻቸዋል"አጼ ሚንሊክ ያደረጉት የልማት ጉዞ የተቀባባ ነበር።የውጭ ቴክኖሎጂን የራሳቸው ከማድረግ ይልቅ የውጭ ሙያተኞችን መጠቀምን እንደ አማራጭ ወሰዱ"የዚህ አባባል ጭብጥ ምን እንደሆነ ለአድማጭ ይቅርና ለራሱ ለመለስ ዜናዊም የሚገባው አይመስለንም። አጼ ምንሊክ እንደማንኛውም ሰው የራሳቸው ደካማ ጎኖች ቢኖሯቸውም በዘመናቸው ለዚያች አገር እድገት ያደረጉት አስተዋጽኦ የሚያስመሰግናቸው እንጂ የሚያስወቅሳቸው አይደለም። ዛሬ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያዊያንን እያባረረ ከጉልበት ሠራተኛ አንስቶ እስከ ዩንቨርስቲ ፕሬዝዳንቶች ድረስ ያሉትን ከውጭ አገር አምጥቶ እያሰራ ባለበት በዚህ ዘመን አጼ ምንሊክን በውጭ ሙያተኞች ተጠቀሙ ብሎ ሲወቅስ ትኝሽም አለማፈሩ የመለስን የጥላቻ ጥልቀት ያመለክታል። ዛሬ አጼ ምንሊክ ቢኖሩ ከመለስ ዜናዊ እጅግ በተሻለ ሁኔታ አገሪቷን መምራት የሚችሉ ሰው መሆናቸውን ታሪካቸው በቂ ምስክር ነው።

መለስ ዜናዊ የአጼ ምንሊክ ልማት የተቀባባ ነው ሲል የአንተስ ልማት ምን አተረፈልን ብለን ብንጠይቅ የምናገኘው መልስ በየአመቱ ከ 14 |አሥራ አራት| ሚሊዮን በላይ ርሃብተኛን ይዛ ለልመና የተሰለፈችን አገር እንጂ ሌላ አይደለም። የአጼ ምንሊክ ልማት የተቀባባ አይደለም። በግዜያቸው ሊሰሩ የሚችሉትን ሰርተዋል። መኪና የሰይጣን ፈርስ ነው ብሎ በሚያስብ ማህበረሰብ ውስጥ መኪና በመሳፈር የሰው ልጅ የሰራው መጓጓዥያ መሆኑን ለህብረተሰቡ ለማስተማር ጥረዋል። ከዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ልቀው ወጥተው ባሰሩት የባቡር ሃዲድ ላይ ዛሬ አዜብ መስፍን ጫት እያመላለሰች እየነገደችበት ነው። ያን ግዜ አጼ ምንልክ የጀመሩትን ስልክ ዛሬ "የምትታለብ ላም ነቸ" ብለው እነመለስ እየፈነጩበት ይገኛሉ። አጼ ምንሊክ ከሃይማኖት ትምህርት ውጭ ሌላ ትምህርትና እውቀት መኖሩን በማያወቅ ህብረተሰብ ውስጥ ሁነው ዘመናዊ ትምህርት ቤቶችን ለማስጀመር ችለዋል። ከጠበልና ከቅጠላ ቅጥል ውጪ ሌላ የህክምና ዘዴ መኖሩን ሰምቶ በማያውቅ ማህበረሰብ ውስጥ ሆስፒታል ለመክፈት አቅሙ የነበራቸው ብርቱ ሰው ናቸው። ልማታቸው የተቀባባ አልነበረም። በወቅቱ አስፈላጊ የሆነና በአስፈላጊው ቦታ ዘርን ማእከል ሳያደርጉ የተጀመሩ ከልብ የሆኑ ልማቶች ነበሩ። መለስ ዜናዊ ለእነዚህ ልማቶች እውቅና አልመስጠቱ የአጼ ምንሊክን ክብር ቅንጣም ታክል አይቀንሰውም።በዚህ ሃያ ዓመት ውስጥ መለስ ዜናዊ ከውጭ አገራት ያገኘው እርዳታና ብድር ኢትዮጵያ በታሪኳ መቸም አግኝታ የማታውቀው ቢሆንም አጼ ምንሊክ ካሰሩት የባቡር ሃዲድ ላይ አንድ ተጨማሪ የባቡር መንገድ እንኳን ሊሰራ አልቻለም። በልመናና በብድር የተገኘውን ገንዘብ በውጭ አገራት ባንኮች ደብቆ አስቀምጦ አጼ ምንሊክን ለመወቀስ መለስ የሞራል ብቃቱ የለውም። ሞሶሎኒ ምንሊክን እንደማያመሰግን ሁሉ ጥቁሩ ሞሶሎኒ መለስ ዜናዊ ምንሊክን ለማመስገን የሚያስችል የሞራል ብቃቱ አይኖረውም። ይሄን ደህና አድርገን እንገነዘባለን።

እንደገናም የጃፓንን እድገት ከአጼ ቴዎድሮስ ጋር እየነጻጸረ የጃፓን እድገት ተሳኪቷል የአጼ ቴዎድሮስ ግን አልተሳካም ብሏል።አሁን በመለስ ዜናዊ የምትገዛው ኢትዮጵያ ግን ከጃፓን ጋር አይደለም መንግስት አልባ ከሆነችው ሶማሊያ ጋር ስትነጻጸር የማትሻልበት ብዙ ነገሮች ያሏት መሆኑን መለስ ዜናዊ መናገር አይፈልግም። ዛሬ ሶማሊያውያን ሳታላይት ቴሌቭዥንን ለማየት የሚያግዳቸው የለም። በሶማሊያ ምድር ሬዲዮኖች ያለምንም አፈና ይሰራሉ። ኢንቴርኔትን ከኢትዮጵዊያን በተሻለ ደረጃ ሶማሌዎች ይጠቀማሉ። በሶማሌ ምድር የሚታፈን ወይም ብሎክ የሚደረግ ድህረ-ገጽ የለም።ዛሬ መለስ ዜናዊ እየገዛ የሚያሰቃያት ኢትዮጵያ ግን ህዝቦች ርስ በራሳቸው የማይተማመኑ፤ ጥላቻና ክፍፍል የነገሰባት፤ አንድነትና አገራዊ ስሜት የጠፋበት፤ በድህነቷና በኋላ ቀርነቷ የምትጠቀስ፤ በሙስና ምሳሌ ሆና የምትታወቅና አጠቃላይ የአገሪቷ የሞራል እሴቶች ተገለው የተቀበሩባት አገር ሆና ሳለች አጼ ቴዎድሮስን ከጃፓን ጋር እያነጻጸረ ሲወቅስ ማን ይጠይቀኛል ከሚል ከንቱ ትእቢት መሆኑን እንረዳለታለን። ይህም የትንሽነቱና ውረድት የሚሰማው ግለሰብ መሆኑን የሚያመላክት መሆኑንም እንገነዘባለን። ይህ ትእቢትና ማን አለብኝነት ግን ለከፋ ውረደት ይዳርገዋል እንጂ የሚያስከብረው ተግባር እንዳልሆነ አሳስበን እናበቃለን።

በመጨረሻም በህዝባቸው መካከል እጅ እየተነሳላቸው ከሚመላለሱና በወቅቱ ከነበረው ማህበረሰብ ጋር በቅርብ የሚተዋወቁ ነገስታትን አንድም ቀን ከቤተ መንግስት ወጥቶ ምን እንደሚመስል እንኳ ታይቶ የማይታወቅ ይህ መንፈሰ ደካማውና ፍጹም ጨካኙ መለስ ዜናዊ በአገራችን አበው ላይ ትችት ሊሰነዝር ምንም ሞራል ብቃት የለውም።እንዲህ ዓይነት ግለሰብም ከስልጣኑ ወርዶ ለፍርድ እስከሚቀርብ ድረስ ትግላችንን አጠናክረን እንቀጥላለን እንጂ በምንም አንፈታም።

መለስ ዜናዊ ሊያጣጥላቸው የከጀላቸውን ነገስታት በዘመኑ የነበረው ህዝብ እንዴት ያያቸው እንደነበርና ምን ዓይነት ቅኔ ይቀኝላቸው እንደነበረ በጥቂቱ አሳይተን ነገራችንን እንቋጫለን።

ለአጼ ቴዎድሮስ እንዲህ የሚል ቅኔ ተደርሶላቸው ነበር፤ **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## ሱዳን ድንበሯን አቋርጠው ወደ ግዛቷ ከገቡት በርካታ ኢትዮጵያዊያን ወጣቶች ወደ 500 የሚጠጉትን በሃይል ወደ አገር ቤት መመለሷ ተገለጸ

የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በአገራችን ውስጥ ባሰፈነው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች ተስፋ ቆረጠው የተሻለ ህይወት ፍለጋ አገራቸውን ጥለው በሱዳን በኩል ከተሰደዱ በአስር ሺዎች ከሚቆጠሩ ወጣት ስደተኞች መካከል ቁጥራቸው ወደ 500 የሚጠጉትን የሱዳን ፖሊስ አሳልፎ ለወያኔ አገዛዝ እንዳስረከበ አንድ የመተማ ነዋሪ ለዝግጅት ክፍላችን በስልክ አስታወቁ።

የወያኔው አገዛዝ ጠረፍ አቋርጠው ሱዳን የሚደርሱ ወጣቶች በብሶት ምክንያት አገራቸውን ትተው በመሄዳቸው የተነሳ ከውጪ ሆነው እየተደራጁ ነው በማለት የሚከሳቸውን አማጽያን እንዳይቀላቀሉ ከፍተኛ ስጋት አድሮበታል ያሉት እኒህ የመረጃ ምንጫችን፤ በመተማ ከተማና አካባቢዋ የሚኖሩ ዜጎች ከመሃል አገር በሁመራና መተማ በኩል ወደ ውጪ እየፈለሱ ያሉትን ወጣቶች ለማስቆም እንዲተባበር መወትወት ከጀመረ ቆይቶአል ብሎአል።

በአገራቸው ተስፋ ቆርጠውና ህይወት ጨልሞባቸው ወደውጪ እየጎረፉ ያሉ ያገሪቱ ዜጎች ከወጣትነት እስከ ጎልማሳነት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ መሆናቸው ሲታወቅ፤ የሴት እህቶቻችን ቁጥር ከወንዶቹ እየበለጠ መምጣቱ፤ በተለይ ደግሞ በሱዳንና ሌሎች የአረብ አገሮች በቤት ሰራተኝነት ለመቀጠር ከወንዶቹ እኩል በረሃውን አቋርጠው ሱዳን የሚገቡ ሴቶች ልጆች በመንገድ ላይ አስገድዶ የመደፈር ችግር ሁሉ እንደሚገጥማቸው ለማወቅ ተችሎአል።

ከመሃል አገር፤ ከጎንደር፤ ከጎጃም እና ከትግራይ ወደ ሱዳን እየፈለሱ ያሉ እነኚህ በአገራቸው ተስፋ ያጡ ወገኖቻችን ድንበር ለማቋረጥ ከአራት አስከ ስምንት ሺህ የኢትዮጵያ ብር ለህገወጥ ደላሎች እንደሚከፍሉ ተያይዞ የደረሰን መረጃ ያመለክታል። የሱዳን ፖሊሲ አስገድዶ ወደ አገራቸው ከመለሳቸው ከነዚህ 500 ያህል ወጣት ስደተኞች መካከል አብዛኞቹ የሁለተኛ ደረጃና የኮለጅ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ሥራ የማግኘት ዕድል ሳያገኙ ቀርተው ለወላጅ ቤተሰብ ሸክም ከመሆን ብለው ስደት የመረጡ እንደሆነ ታውቆአል።

የመለስ ዜናዊ ዘረኛ ፖሊሲ በቀፈቀፈው የኢኮኖሚ፤ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ምክንያት የወደፊት ተስፋቸው ጨልሞ አገራቸውን በየብስ፤ በምድርና በባህር አያቋረጡ የሚሰደዱ ስደተኞች ቁጥር ባለፈው 10 አመት እጅግ እንደጨመረ የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን ሪፖርት ያመለክታል።

## በኢትዮጵያ ሚሊየኖች ይራባሉ፣ ነገር ግን የውጪ ሃገራት ኢንቨስተሮች . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የተባበሩት መንግሥታት በኢትዮጵያም ሆነ በአካባቢው የአፍሪቃ ቀንድ ሃገራት እየታየ ስላለው ረሃብ ለበርካታ ወራት ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ የቆየ ሲሆን፡ በቂ ምርት አለመኖርና በአካባቢው ያለው የእርስ በርስ ግጭት የምግብ እጥረትን ሊያስከትሉ እንደሚችሉ፣ አገሮቹም ሆኑ ወዳጆቻቸው እንዲያስቡበት ጥሪ እንዳደረገና በአሁኑ ወቅት በአካባቢው ለተከሰተው ከፍተኛ የሆነ ረሃብና ለሚጠፋው የሰው ልጅ ሕይወት ተጠያቂዎቹ የየሃገራቱ መንግስታት ናቸው የሚል አይነት መልዕክቶችን በማስተላለፍ ላይ ነው፡፡

የወያኔ መሪዎች በ1977 በአገራችን ሰሜን ክፍል ተከስቶ የነበረውና በአገሪቱ ላይ አሉታዊ ገጽታውን ጥሎ ያለፈው አስከፊ ድርቅና ረሃብ ዳግም ላይከሰት ተቆጣጥረነዋል በማለት በባዶ ፕሮፖጋንዳ ሲያደነቁሩን ከኖሩ በኋላ በታሪካችን ረሃብ ታይቶበት ወደማይታወቅበት ደቡብ የአገራችን ክፍል ተዛምቶ ቢያንስ ላለፉት 10 አመታት በየአመቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩት ዜጎች ህይወት እየቀጠፈ ይገኛል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የምግብና እርሻ ድርጅትን ጠቅሶ ዘ ጋዜት እንደዘገበው ደግሞ፣ እስካሁን ባለው ሁኔታ የሟቾች ቁጥር በአሥር ሺዎች መቆጠር ጀምሯል፡፡

ይህ በንዲህ እያለ ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ያሉ የርሃብተኞችን ቁጥር እየደበቀ መሆኑ እየተዘገበ ሲሆን፣ ድርቅ በተከሰተባቸው አካባቢዎችም የዓለም አቀፍ ሚዲያም ሆነ የርዳታ ሰጪ ድርጂቶች እንዳይገቡ መከልከሉ ታውቆአል። በወያኔ የልማት ፖሊሲ አርሶ አደሩ ትርፍ ምርት እያመረተ ሚሊየነር ሆኖአል በማለት የሚደሰኩረው የአረመኔው መለስ ዜናዊና ግብረአብሮቹ ቡድን እራሱ በፈጠረው የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የተከሰተውን ረሃብ በተፈጥሮ ድርቅ በማሳበብ ላይ እንደሚገኝ፤ ገመናውንም ለመደበቅ ሲል ዓለም አቀፍ የዜና አውታሮች መንግሥት አልባ በሆነቺው ሶማሊያ ላይ ብቻ እንዲያተኩር ለማድረግ ሌት ከቀን እየሰራ እንደሆነ ታውቆአል።

ዘረኛው አገዛዝ ህዝብ እንዲህ በረሃብ እንደቅጠል እየረገፈ በሚገኝበት ወቅት በመቶ ሚሊየኖች የሚቆጠር ዶላር በማውጣት የጦር ታንኮችን መግዛቱን መዘገባችን ይታወሳል።

## የከፍተኛ ትምህርት ተቋዋማት የትምህርት ጥራት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በሌላም በኩል በሶሺዮሎጂ የትምህርት መስክ የሁለተኛ ዲግሪዉን የያዘ ስሙ እንዳይጠቀስ ያሳሰበ ወጣት፣ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋአማት የትምህርት ጥራት ደረጃ በአሳፋሪ መልኩ የወደቀው ዛሬ ሳይሆን ከበርካታ አመታት በፊት ነው። ይህ የትምህርት ጥራት ሲወድቅና እንዲህ ባለ አሳፋሪ ደረጃ ላይ ሲገኝ በተለይም በከፍተኛ ትምህርት ውስጥ የሚገኙት ምሁራን ተብየዎች እጃቸውን አጣጥፈው ሲመለከቱ ቆይተዋል። አሁን ባለንበት ሁኔታ በምን መልክ ይህን ችግር መፍታትና ወደነበረበት ደረጃ መመለስ እንደሚቻል አይገባኝም። ይህቺ ሃገር በአይናችን እየተመለከትናት በሁሉም ዘርፍ ልተወጣበት ከማትችልበት አዘቅት ውስጥ እየገባች ነውና ችግሩን ለመቅረፍ ባለመጣራችን ሁላችንም በታሪክና በተተኪው ትውልድ ፊት በሃላፍነት ከመጠየቅ የምንድን አይመስለኝም ብሎአል።

በዘንድሮው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ምረቃ ላይ የተገኘው ሆድ አደሩ ጁነዲን ሳዶ የትምህርት ጥራት ችግር ከመምህራን ብቃት ጋር ተዳምሮ ተማሪዎችን በብቃት የማውጣቱ ሥራ ገና የሚቀረው ነው ፣ ድህነትን ልናጠፋ የምንችለው የምስክር ወረቀት ያላቸው ሥራ ፈላጊዎችን ማፍራት ሳይሆን፣ ሥራ ፈጣሪና ብቃት ያላቸውን ተማሪዎች በማፍራት ነው በማለት መደስኮሩ ታውቋአል።

የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ጁነዲን ሳዶ ባደረገው ንግግር ላይ አስተያየት እንዲሰጡት የጠየቃቸው የአንዲት ተመራቂ አባት በሰጡት አስተያየት፣ እንደ ጁነዲን ሳዶ ያሉት የወያኔ ሆድ አደሮች እኮ የሚናገሩትን የሚያውቁም አይመስለኝም፣ በሃገራችን ውስጥ እየታዩ ላሉ በርካታ ችግሮች መንስኤዎቹ እነሱ፣ ይህ መሆኑን እያወቁ ደግሞ፣ ልክ እንዳሁኑ የትምህርት ጥራት ደረጃ አሳቢ ነው በማለት ባደባባይ መናገር የወያኔ ባለስልጣናት ምንም አይነይት ይሉኝታና ሃፍረት ያልፈጠረባቸው መሆኑን ከማሳየት ውጪ ምንም የሚፈይደው ነገር የለም ብለዋል።

## አረመኔው የወያኔ አገዛዝ ከኤች አይቪ ቫይረስ ጋር . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

መድኃኒቱን አንድ ቀን ሳይወስዱ ካደሩ ሲዲፎራቸው እንደሚጨምር የገለጹት ሠራተኛዋ፣ ነፍሰጡሮች መኖራቸውንና ወደ ሌላ ክሊኒክ ወይም ወደ ሆስፒታል ለመሄድ ከመሥርያ ቤቱ ክሊኒክ ሪፈር ማጻፍ እንዳለባቸው እየታወቀ፣ ከመሥርያ ቤቱ ጋር ያላቸው ጉዳይ እልባት ሳያገኝ "አትገቡም" መባላቸው ለበቀል የሚያነሳሳ መሆኑን በመግለጽ ቦርዱ በአስቸኳይ ውሳኔ እንዲሰጣቸው መጠየቃቸውም በዚሁ ዘገባ ላይ ተመልክቱአል፡፡

ከኤችአይቪ(ኤድስ ጋር የሚኖሩት ሠራተኞች ችግራቸው ታይቶ ደመወዛቸው እየተከፈላቸው በሒደት ሥራውን እንዲያቆሙ አለመደረጉ እንዳሳዘናቸው በመግለጽ፣ ሕይወታቸውን ለአደጋ በማጋለጥ ለበርካታ ዓመታት ከሠሩበት መሥርያ ቤት ወጥተው መጣላቸው ሳያንስ፣ ዓለም ሳይቀር የሚረባረብበትንና ስርጭቱን ለመግታት ትኩረት ሰጥቶ የሚሠራበትን ኤችአይቪ/ኤድስን ትኩረት መንፈግ አግባብ ባለመሆኑ፣ ቦርዱ በአስቸኳይ ትዕዛዝ እንዲሰጥላቸው መለመናቸው ታውቋአል፡፡ "እንኳን ደመወዝ ታግዶብን ተከፍሎንም መኖር አቅቶናል፡፡ የኤችአይቪ/ኤድስ መድኃኒት ያለምግብ መውሰድ አይቻልም፡፡ ከባድ መድኃኒት ነው፡፡ ልጆች አሉን፣ የቤት ኪራይ እንከፍላለን፤" ያሉት ሠራተኛዋ፣ ከብሔራዊ ኤችአይቪ/ኤድስ ሴክሬታሪያትና ከሌሎችም ቦታዎች የተሰጡዋቸው ንብረቶች መኖራቸው በክሊኒኩ እንዲጠቀሙ እንዲፈቀድላቸው ጠይቀዋል፡፡

በዘረኛውና አምባገነኑ አገዛዝ ቁንጮ መለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን አማካኝነት በመቶ ሚሊየኖች የሚቆጠር ገንዘብ እየተዘረፈበት ያለው የኤች አይ ቪ ኤድስ ችግር በኢትዮጵያ አሁንም ከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ በርካታ ታማሚዎች ተገቢ የሆነ ርዳታ ሊያገኙ ባለመቻላቸው ህይወታቸው በየ እለቱ እየተቀተፈ እንደሚገኝ በስፋት ሲዘገብ መቆየቱ ይታወሳል።

## መለስ ዜናዊና የቀደሙት ነገስታት. . . (ከገጽ 3 የዞረ)

*ገደልን እንዳይሉ ሙተው አገኟቸው፤*
*ማረክን እንዳይሉ ሰው የለ በጃቸው፤*
*ምን አሉ እንግሊዞች ሲገቡ አገራቸው።*

ይሄ እንግዲህ አጼ ቴዎድሮስ ለጠላት እጄን ከምሰጥ ብለው በገዛ ሽጉጣቸው ራሳቸውን የገደሉ ግዜ የተደረሰላቸው ቅኔ ነው።

ለአጼ ምንሊክ፤

*ምኒልክ ተወልዶ ባያነሳ ጋሻ፤*
*ግብሩ እንቁላል ነበር ይህን ግዜ አበሻ።*
*በሰራው ወጨፎ ባመጣው እርሳስ፤*
*ተፈጠመ ጣሊያን አበሻ እንዳይደርስ።*

አጼ ምንሊክ አድዋ ላይ ድል ቀንቷቸው ወደ ሸዋ ሲመለሱ የተቀኙላቸው ነው።

አጼ ዮሃንስ በመተማ በተደረገው ጦርነት ድል ተመትተው የሞቱ ግዜ አንዱ እንዲህ ሲል ተቀኘላቸው።

*በደንቢያ መታረድ አዝኖ ዮሃንስ፤*
*ደሙን አፈሰሰ እንደ ክርስቶስ።*
*እንዳያምረው ብሎ ድኻ ወዳጁን፤*
*መተማ አፈሰሰው ዮሃንስ ጠጁን።*

ዜጎች ይሄን መሰሉን ቅኔ እየተቀኙ በወቅቱ ለነበሩት ነገስታት ፍቅራቸውንና ክብራቸውን ይገልጡ ነበር። አሁን መለስ ዜናዊ እንዲህ ያለ የህዝብ ፍቅርና ክብር አለው ወይ ብለን መጠየቅ ፈልገን ነበር። ሆኖም ግን መለስን ከእነዚህ ሰዎች ጋር ማወዳደር እንደ አንድ አገር ወዳድ ነኝ እንደሚል የዋህ አምባገነን ስለሚያስቆጥረው ጥያቄውን ትተነዋል። የህዝብ ጠላት የሆነን ይህን ጨካኝ ግለሰብ ከነገስታቱ ጋር ማወዳደር የማይገባውን ክብር መስጠት ነው። መለስ ዜናዊ ከእነዚህ ሰዎች ጋር ለማነጻጸር የሚያበቃ ስብእና የለውም። ነገራችንን በዚህ አበቃን። ቸር እንሰንብት።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz
እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:00 እስከ 2:30 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን። **ማሳሰቢያ**:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org